# ለካስ ሰው ኖረሃል!
(ለጥላሁን ገሠሠ)

ከ ባዩ በየነ
(ቶሮንቶ ካናዳ)

በትንፋሽህ ማዕበል ናውጠን
በድምፅህ ሱናሜ ተንጠን
በዜማህ ገሞራ ቀልጠን
በትዝታህ ውቅያኖስ ሰምጠን
አምሳ ዓመት ሙሉ ላልጠገብንህ
'በቃን ነደድን' ላላልንህ...

*ለኛ ነው ማልቀስ ወይኔ*
*ለኛ ነው ማለት መጥኔ!፤*

ስታንስቀስቀን፣ ስታንከተክተን
ስታንፈቀፍቀን፣ ስታብከነክነን
ጥለህ ስታነሳን ፣አንስተህ ስትጥለን
ሠማይ ስታጎነን ፣ምድር ስታፈርጠን
እንደባለውቃቢ ፣ስታርገፈግፈን
ሥምክን እየጠራን ስንምል የኖርን
ፈጣሪ መስለኸን፣ ነበር ያመለክንህ
ለካስ ሰው ኖረሃል፣ ሞት የሚያሸንፍህ...

*ማዘንስ ለኛ ነው፣ ጌታን ላስቀየምነው*
*ተሰባሪውን ሰው፣አምልከን ለኖርነው፤*

ከሆንክ ሰውማ፣ ሞትህ ካልቀረማ
ነጋቲ ጋ ጥሌ፣ ያ ሰገሌ ደ'ማ
ያ ሞቲ ሙዚቃ፣ ሁሌ ጃለተማ
'ልሂድ' ካልከንማ
የዘፋኞች ማማ
በል 'ደህና ሁን'ማ ።

April 23/2009 —Toronto, Canada

(በዚህ አጋጣሚ በቶሮንቶ ከተማ የሚገኘው የሐዲስ-ንጋት የኪነ-ጥበብ መድረክ የተሰማውን ጥልቅ ኀዘን ለጥላሁን ገሠሠ ቤተሰብና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይገልፃል)